# የዕድር የሃይማኖት መቻቻል መልኮች በበቆጂ ከተማ

ፍሬህይወት ባዩ

**አኅጽሮተ ጽሁፍ**

*ዕድር በሀገራችን የተለመደና በተለይ የቀብር ስርዓት እና ተያያዥ ተግባራትን በመተጋገዝ ለመከወን ተቀራርበው የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች በፈቃደኝነት የሚመሰርቱት ባህላዊ ተቋም ነው። ዕድር በኢትዮጵያ ውስጥ በአብዛኛው ህዝብ ዘንድ ለተመሳሳይ አላማ በየጊዜው የሚቋቋም ታዋቂ ባህላዊ ተቋም ሲሆን በበቆጂ ከተማ ነዋሪዎች ዘንድ ከ1941 ዓ.ም ጀምሮ የሚታወቅ ተቋም ነው። በርእሱ የተጠቀሰው የጥናቱ ዋና ዐላማ በበቆጂ ከተማ አስተዳደር የተቋቋሙ ዕድሮችን ምንነት በመግለጽ የተለያየ ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ ዕድርተኞች ተቻችለው የአንድ ዕድር አባል በመሆን የሚኖሩበትን ዘዴ ከፎክሎር ጥናት አኳያ ይተነትናል። መረጃዎቹ በመስክ በመገኘት በምልከታ፣ በቃለ-መጠይቅ፣ በቡድን ውይይት እና በሰነድ ምርመራ ዘዴ የተሰባሰቡ ናቸው። በጥናቱ የተገኙ መረጃዎች እንደሚያሳዩት የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖቶች ተከታይ ማህበረሰቦች ዕድሮችን በጋራ ይመሠርታሉ፡፡ አንድ ዕድር ሲመሰረት የሚቀራረቡ፣ ሰዎች በፈቃደኝነት ተሰባስበው በተወሰነ ጊዜ በመገናኘት ገንዘብ በማዋጣት የሚመሰርቱት ተቋም ነው። የሁሉም ዕድሮች ዋና አላማ አባሉ፣ የቅርብ ዘመዱ ፣ ቤተሰቡ ወይም እራሱ በሞት ሲለይ በተለያየ መልኩ ሀዘንተኛው ለመርዳት ነው፡፡ ሁሉም ዕድሮች በጽሁፍ የሰፈረ መተዳደሪያ ደንብ አላቸው። ደንቦች የያዙት ዋና ዋና ነጥቦች፡- የዕድሩን አላማ፣ በአባልነት የሚካተቱ ግለሰቦች ማሟላት ስለሚገባቸው መስፈርት፣ የአባላቱ መብትና ግዴታ፣ የዕድሩ አስተዳደር አካል ማንነት፣ መብትና ግዴታ እና ተያያዥ ጉዳዮችን የያዘ ነው። በዚሁ መሠረት አንድ የእድሩ አባል ወይም የቅርብ ዘመድ ሲሞት ዕድርተኛው፤ የሟችን አስከሬን ወደ መቃብር በክብር በመሸኘት ከመቃብር መልስ እስከ ሶስት ቀን የሟችን የቅርብ ዘመዶች በማጽናናት በጉልበት፣ በገንዘብ፣ በቁሳቁስ እና በመሳሰሉት ማገዝ ነው። የዕድሮቹ አደረጃጀት በአንድ ሰፈር የሚኖሩ የመሰረቱት፣ የሰፈር ዕድር ሲባል ይህም የወንዶችና የሴቶች(ወይም የሴቶች ባልትና) ተብሎይለያያል። በከተማ ውስጥ ነዋሪ የሆነውን ሁሉ የሚያካትተው ትልቁ ዕድር ይሉታል። በበቆጂ ከተማ ከ1982 ዓም በኋላ የዕድር ክፍፍል የእድሩ አባል በሚከተለው ሃይማኖት ምክንያት ልዩነት አምጥቷል። ልዩነቱም የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታዮች በአብዛኞቹ ዕድሮች አባል መሆን አለመቻል ነው። በዕድርተኞች መካከል የሚከወኑ እሴቶች ደግሞ መቻቻል ከሚያካትታቸው ባሕርያት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው ተቻችለው የሚኖሩ የተለያየ ሃይማኖት ተከታዮች እንዳሉት ሁሉ አለመቻቻል የታየባቸው እንዳሉም ይጠቁማል።*

## 1. መግቢያ

ከግጭቶች መነሻ አንዱ ተቀራርበው በሚኖሩ ህዝቦች መካከል ልዩነትን ብቻ በማጉላት ትስስራቸው እንዲላላ ብሎም ወደ ግጭት እንዲያመሩ ማድረጉ ነው።

ጥናቱ ትኩረት ያደረገው በአርሲ ዞን በበቆጂ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ ዕድሮች ላይ ነው። አርሲ ዞን በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ሥር ከሚገኙ አስራ ስምንት ዞኖች አንዱ ነው። ከ1998ዓ.ም ጀምሮ አርሲ ዞንና ምእራብ አርሲ በሚል ለሁለት ተከፍሏል። የምእራብ አርሲ ዋና ከተማ ሻሸመኔ ሲሆን የአርሲ ደግሞ አሰላ ነው። የአርሲ አስተዳደራዊ መዋቅሩ በ24 የከተማ አስተዳደርና በ497 የገጠር ቀበሌዎች የተከፈለ ነው። አዋሳኞቹም በምስራቅ ሀረርጌ፣ በሰሜን ምስራቅ ሸዋ፣ በደቡብ ባሌ ዞን፣ በምእራብ ደግሞ ምእራብ አርሲ ይገኛሉ።

የበቆጂ ከተማ አስተዳደር ከዋና ከተማው አሰላ 54 ኪ.ሎ ሜትር፤ ከአዲስ አበባ በስተ-ደቡብ በ232 ኪ.ሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል። የከተማው ነዋሪዎች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን (የኢ.ኦ.ተ.ቤ)፣ የእስልምና እና የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው።

የበቆጂ ማዘጋጃ ቤት ሌሙና ቢልቢሎ ወረዳን ምስረታ በተመለከተ ያዘጋጀው ጽሁፍ "በቆጂ ከተማ የተቆረቆረችው በ1929 ዓ.ም አካባቢ ነው። ከተማ እንድትሆን ምክንያት የሆናት የኢጣልያን ወረራ ነው (1999፡ 2)። ይህ ማለት ግን ከዚያ በፊት በቆጂና ዙሪያዋ ጠፍ መሬት ነበር ለማለት አያስደፍርም። ምክንያቱም ከከተማዋ ከ5 እስከ 14 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ የሚገኙ መንደሮች ከከተማዋ ምሥረታ በፊት ነበሩ። ለምሳሌ ከከተማዋ ሰባት ኪ.ሎ ሜትር ርቀት ላይ "ሌሙ ቡርቂቱ" የተባለ የገጠር ቀበሌ በ1903 ዓ.ም ተቆርቁሮ ነበር። ለዚህ ማስረጃ የሚሆነው ሌሙ ማርያም ቤተ-ክርስቲያን ከ1902 ዓ.ም በፊት መኖሯ ነው። በግምት ከከተማዋ 8 ኪ.ሎ ሜትር ርቀት ላይ ደግሞ "በዲ ሚካኤል" የተባለው ቤተ-ክርስቲያን የተሰራው በ1915 ዓ.ም ነው (ፍሬሀይወት 2000፡ 10)፡፡

የበቆጂ ከተማ ነዋሪዎች የተለያዩ ማህበራዊ መስተጋብሮች አሏቸው። ማህበራዊ መስተጋብሮቹ በኑሮ ውስጥ አንዱ ወደ ሌላው በተለያዩ ምክንያቶች በመሄድ እና የግል ችግሮችን በጋራ ለመፍታት ከመነጨ ፍላጎት የመጡ ናቸው። ከማህበረሰቡ የጋራ መስተጋብር ማሳያ አንዱ ዕድር ነው። ሃይማኖት ድንበር ሆኖ ሳያግዳቸው በሰላምና በወዳጅነት ማህበረሰቡ አብሮ በመኖር በገሀዱ ዓለም የፈጠራቸውን የመቻቻል እሴቶች ከፎክሎር ዕይታ አንፃር ለማጥናት የባለሙያዋ አካባቢውን በቅርበት ማወቅ መረጃዎችን ለማግኘት አመቺ በመሆኑ ርዕሰ-ጉዳዩን ለመምረጥ ምክንያት ሆኗል።

በዚህ ጥናት የተመለሱ የምርምር ጥያቄዎች፣ በበቆጂ ከተማ አስተዳድር የሚኖሩ የክርስትና እና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች የመሰረቷቸው ዕድሮች ምንነትእና የመቻቻል ፎክሎር መገለጫ ገጽታቸው፣ ምንድን ነው? የሚል ነው።

የጥናቱ አላማ፣ በበቆጂ ከተማ አስተዳደር በክርስትና እና በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች መካከል በረዥም ጊዜ መስተጋብር የተፈጠረውንና የዳበረውን ዕድር ምንነትና የመቻቻል መገለጫነቱን ማሳየትና መተርጎም ነው።

የጥናቱ ጠቀሜታ፤ የተለያዩ ሀገራዊ እሴቶችን በተለይም ማህበረሰቡ ችግሮችን በግለሰብ ደረጃ ሳይሆን በጋራ ለመፍታት አስቦ ቀድሞ ለዘመናት የዘለቀ ተቋም ማጥናት የተለያዩ ጠቀሜታዎች አሉት። በተለይም እንደ ዕድር ያሉ ባህላዊ ተቋማት የተለያዩ ሃይማኖቶች ያሏቸው ሀገሮች በልዩነቶች ምክንያት ወደ ግጭት እንዳይገቡ የመከላከል አቅም አላቸው። በበቆጂ ከተማ አስተዳደር ያሉ ዕድሮች በመላው ሀገሪቱ ውስጥ በተመሳሳይ ይዘትና ቅርጽ አሉ። ስለዚህ ይህ ጥናት አንዱን አጥንቶ መልካሙን ለመውሰድ እና በሌላም ቦታ ያሉትን ለማጥናት ጥቅም ላይ ለማዋል ያግዛል። በግለሰቦች፣ በማህበረሰቦች መካከል ያለን የሃይማኖት ልዩነት ወደ ጎን ብሎ አንድነትን የፈጠረበትን የመቻቻል እሴት ማጥናት ጠቃሚ ባህላዊ እሴቶች ለማሳየት ይህ ጥናት ጠቀሜታ ይኖረዋል።

## 2. የጽንሰ ሀሳብ መነሻ እና የጥናቱ ዘዴ

### 2.1 መቻቻል

መቻቻል፤ ኪዳነወልድ "መቻቻል" የቃል ክፍሉ ስም ሲሆን ትርጉሙም መስማማት እንደሆነ ይገልፃሉ (ኪዳነወልድ፣ 1948፣ 522)። ይህንኑ ቃል ግሱ ወይም የመቻቻል መነሻው "ቻለ" ሲሆን ተመሳሳይ ቃሉ ተሸከመ፣ ወሰነ፣ ያዘ...የሚል ነው።

መቻቻልን በፅንሰ ሀሳበ ደረጃ እንዲህ ነው ብሎ ለመተንተን ከመሻት ይልቅ በሁለት ቡድኖች ወይም ግለሰቦች መካከል ባለ አወንታዊ ወይም አሉታዊ ግንኙነት በመመሥረት በሚከናወኑ ተግባቦቶች ላይ በሚደረግ የፎክሎር መረጃ መተንተን መግለፅና መገንዘብ ይበልጥ ምንነቱን የሚያስረዳ ይሆናል። መቻቻል በዘወትራዊ ህይወት ውስጥ የሚመሠረት ተግባር ነው። ለምሳሌ የተለያየ ሃይማኖት በሚከተሉ ማህበራዊ ቡድኖች መካከል ባለ የግንኙነት ባህርያት ላይ አተኩሮ የሚፈጠር ሊሆን ይችላል። የመቻቻልን ግንዛቤና ባሕርያት በተቃርኖ ባለመቻቻልና በመቻቻል ገጽታዎች አንዱ ስለሌላው ያለውን ሀሳብ አስተያየትና አመለካከት ማለትም በአውዳዊ ብያኔዎች ለማነፃፀርና ለመገንዘብ ይቻላል።

መቻቻል ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ባላቸው የሃይማኖት ልዩነት ብቻ የሚታይ ጽንሰ ሃሳብ ሳይሆን በግለሰቦች እና በቡድኖች መካከል ባሉ ሌሎች ልዩነቶች የሚታይ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም ከሃይማኖት ጋራ የማይያያዙ ብዙ ዓይነት የመቻቻል የህይወት ገጽታዎች አሉ(Newman, 1978 99)። ለዚህ ጥናት የተመረጡት የማህበረሰብ ክፍሎች ልዩነታቸው የሚከተሉት ሃይማኖት ይሆናል። መቻቻል የሚለው ጽንሰ ሀሳብም የሚቃኘው መቻቻሉ ተጠኚው ማህበረሰብ በሚመራበት የሃይማኖት ልዩነት ሳይታጠር ባለው መስተጋብር የተፈጠሩ ባህላዊ እሴቶች መካከል አንዱ በሆነው ዕድር ላይ ይሆናል።

በአጠቃላይ ይህ ጥናት የሃይማኖት መቻቻል ለሚለው ጽንሰ ሀሳብ ብያኔ መሠረቱ ለሌላው መጥፎ አመለካከትና ጥላቻ ሳይፈጥሩ፣ ተሳስቦ፣ ተከባብሮ፣ ተስማምቶ መኖርን እንዲሁም አንዱ ለሌላው ያለውን በጎ አመለካከት ሁሉ ያካትታል። አንድ ሰው የራሱ ሃይማኖት "እውነት ነው! ትክክል ነው!" ብሎ እንደሚያምነው ሁሉ የሌላውም ሃይማኖት "ለአማኙ እውነት ነው! ትክክል ነው!" ብሎ በማመን መቀበልና ማክበር የመቻቻል ባሕርያት ናቸው (Newman 1978: 194)። ይህ ካልሆነና የሌላው ሃይማኖት መጥፎ፣ "የእኔ ሃይማኖት ብቻ ልክ ነው!" ከተባለ ከሌላው ሃይማኖት ተከታይ ጋር አለመቻቻልን ይፈጥራል። ምክንያቱም "ልክ የሆነው የእኔ ስለሆነ፤ የእኔን ተቀበለኝ!" ወደሚለው አስተሳሰብ ያመራል፡፡

**2.2 የጥናቱ አይነትና ዘዴ**

የጥናቱ ዘዴ የአይነት ወይም የትርጉም ባህርይ ያለው ነው። ከመስክ የተሰበሰበ መረጃ የጥናቱ ዋንኛ የመረጃ ምንጭ ነው። መረጃ ለማሰባሰብ ምልከታ፣ ቃለ-መጠይቅና የቡድን ውይይት ዘዴዎች በአውዳዊ ሁኔታ በአገልግሎት ላይ ውለዋል። ምልከታ የተደረገው የዕድር አባላቱ በሚሰባሰቡበት ቦታ በመገኘት በቃለመጠይቅ እና በቡድን ውይይት እንዲሁም በሰነድ ፍተሻ የተመለሱ ተጨማሪ ጥያቄዎች ተገኝቶባቸዋል። በቃለ-መጠይቅ የእድሮቹን ታሪካዊ ሂደት የተከሰቱ ለውጦችን ለናሙና የተወሰዱ ዕድሮችን አመሰራረት በተለይም የሃይማኖት መቻቻል በዕድርተኞች መካከል የሚታይባቸውን መልኮች በተመለከተ መረጃ የተገኘው በዚህ ዘዴ ነው። በቡድን ውይይት በተለይ ከ1982ዓ.ም በኋላ የዕድርተኛውን ሃይማኖት የሚመለከት ደንብ የወጣበትን ምክንያት ለማጣራት ከየእድሩ የተውጣጡ፣ በወቅቱ የነበሩ የዕድር መስራቾችና የእድሮቹ አስተዳዳሪ ሆነው የሰሩ ግለሰቦችን ባካተተ የቡድን ውይይት መረጃዎች ተሰብስበዋል። ከቤተ-መጻህፍትና ከተለያዩ ቦታዎች የተገኙ የጽሁፍ መረጃዎች ከመስክ ለተገኙ መረጃዎች ማመሳከሪያ በመሆን አገልግለዋል።

በንባብ ዳሰሳ ውስጥ የበለጠ ቅርበት ያላቸው ዕድርን ብቻውን ወይም ከተለያዩ ርእሰ ጉዳዮችጋር አያይዘው ያጠኑ አሉ። አርሲ ላይ በሃይማኖት መቻቻል ላይ የተሰራ ጥናትም ሆነ የተጻፈ መረጃ የለም። ዕድሮችን በተመለከተ የተጠኑ ጥናቶች በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ ዕድሮች መካከል የዕድርን ማህበራዊ ጠቀሜታ በተመለከተ ጥናቶች በተለያዩ የትምህርት ክፍሎች ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ተጠንተዋል[1]። የዕድርን ታሪካዊ መሰረት በተመለከተ በኢትዮጵያ ጥናት ተቋም ላይ ለህትመት የበቁ ጥናቶች አሉ ከነዚህ መካከል አንዱ የአሉላ ስራ ነው[2]። እኚህ አጥኚ በ1958ዓ.ም ከሌላ አጥኚ ጋር ዕድር በኢትዮጵ ውስጥ እንዴትና መቼ ተጀመረ የሚለውን ለመመለስ አጥንተው ለህትመት አብቅተዋል። በተጨማሪም ሶስተኛ ጥናታቸውን በ2010ዓ.ም ከሌላ አጥኚ ጋር በኤች አይ ቪ ኤድስ ምክንያት ወላጅ አልባ የሆኑትን ቤተሰቦች በማገዝ ዕድር በአዲስ አበባ የነበረውን ሚና አጥንተዋል። ሌላው ዕድርን በተመለከተ ከምጣኔ ሀብት[3] ጋር

[1] Shiferaw Tesfaye, 2002.
[2] Alemayehu, Seifu 1968; Alula, Pankhurste (ed).2003
[3] Dejene, Aredo; 2010

አያይዞ አጥንቷል። እንዲሁም በከንባታና ወላይታ አርብቶ አደር በሆኑት የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ የዕድርን ሚና በተመለከተም ተጠንቷል4። የጥናቱ ዞን በሆነው አርሲም ሆነ በበቆጂ ከተማ አስተዳደር ላይ ዕድርን አስመልክቶ የተጠና ጥናት የለም። በተጨማሪም ዕድር ከሃይማኖት መቻቻል አኳያ በጥናቱ አካባቢም ሆነ እንደ ሀገር ለዚህ ጥናት ተዛማጅ ጥናቶች በተደረገበት በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ቤተ-መጻህፍት እንዲሁም በድህረ ገጾች በአጠቃላይ ዕድርን ከሃይማኖት መቻቻል ጋር አያይዞ የተጠና ጥናት አልተገኘም።

## 3.የዕድር፣ የሃይማኖት መቻቻል መገለጫነት

በኢትዮጵያ ውስጥ ዕድር በዚህ ቦታ፣ በዚህ ዘመን፣ በዚህ ዓይነት አጋጣሚ ተጀመረ የሚል ትክክለኛ መረጃ አይገኝም።5 ይሁንና በበቆጂ ከተማ አስተዳደር ነዋሪዎች ዘንድ የመጀመሪያው ዕድር በ1941ዓም ተመስርቷል።

በበቆጂ ከተማ የሚገኙ ዕድርተኞች 'ዕድር' ወይም 'ሸንጎ' በሚል ሁለቱንም መጠሪያ በተለዋዋጭነት ይጠቀሙበታል እንጂ የትርጉም ልዩነት የለውም። በተለይ ሸንጎ የሚለው የተለመደ እና ለዚህ ጥናት መረጃ ሲሰጡ፣ እንዲሁም በጽሁፍ በሰፈሩ ደንቦች ላይ ከዕድር ይልቅ "ሸንጎ" የሚለውን ቃል ይጠቀማሉ። ዕድር አባላቱ በፈቃደኝነት የሚመሰርቱት፣ በመተሳሰብ የሚረዳዱበት፣ የሚተጋገዙበት፣ የሚማማሩበት፣ አንዱ የሌላውን ችግር የሚካፈልበት እና ለቀጣዩ ትውልድ አውርሰው የሚያልፉት ማህበራዊ ተቋም ነው፡፡ ዕድርተኞች ዕድርን ከሀዘን ጋር አያይዘው ይገልጹታል፡፡

አንድ መረጃ ሰጭ ዕድርን ሲገልጹ፡- "ዕድር ማለት ስሞት ቀባሪዬ ስለሆነ ደግ ጎረቤቴ ነው፣ በችግር ቀን ከዘመድ ቀድሞ ደራሽ ነው፡፡ ብሞት ማን ይቀብረኛል ብዬ ኣላስብም። የከፈን ልብስ ገዝቶ አንቀባሮ የሚቀብር ዕድር አለኝ"6 ይላሉ፡፡ ሌላዋ መረጃ ሰጭ በተመሳሳይ፡-"ዕድር፣ ልጅ የሌለውን፣ ባለ ልጁንም፣ ሙስሊም ክርስቲያን ሳይል፣ ሁሉንም ዕድርተኛ በእኩል የሚቀብር ገመና ከታች ነው፡፡ ዕድር የሌለው ሰው አለሁ ሊል አይችልም"7 በማለት ለሁሉም ሰው አለው ያሉትን ማህበራዊ ዋጋ ገልፀዋል፡፡

---

[4] Thomas Leonard; 2013.

[5] እስካሁን የተካሄዱት አንዳንድ ጥናቶች 'ተጨማሪ ጥናት ያስፈልጋል' ከማለት በስተቀር የደረሱበት ግኝት የለም። ለምሳሌ (Alula 2003፡358) በኢትዮጵያ ውስጥ ቀዳሚ ታሪክ ያላቸው የዕድር ጀማሪዎች በደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኙ የጉራጌ ማህበረሰብ አባላት መሆናቸውን ይጠቅሳሉ፡፡ ሆኖም ይህን ከመግለፅ ውጭ ጥናቱ በምን ባህላዊ ትውፊት ላይ ተመሥርቶ የትኛው የጉራጌ ክፍል፣ መቼ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ዕድርን እንደመሠረተ የሰጠው ማረጋገጫ የለም። ይህን የእነ አሉላን ሀሳብ በመቃወም የጉራጌ ማህበረሰብ ዕድርን ጀመረ ለማለት ምንም ዓይነት ማስረጃ የለም። ምክንያቱም በጉራጌ ማህበረሰብ ዘንድ ያለውን የዕድር ዓይነት ልምድ ያላቸው ሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች አሉ በማለት ያስረዳል (Alemayehu, 1968: 8)፡፡ ሆኖም በዚህ ቦታ፣ በዚህ ጊዜ፣ እነ እከሌ ጀመሩት በሚል ያመለከተው የለም፡፡

[6] መረጃ ሰጭ፤ ወ/ሮ እመቤት ከበደ፣ እድሜ 74፣ የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታይ፣ በንግድ ሥራ የሚተዳደሩ የእግዚአብሄር አብ ዕድር ዳኛ (ቃለ መጠይቅ፣ በቆጂ ፣ ህዳር 14 2006)፡፡

[7] መረጃ ሰጭ፡- ወ/ሮ ኡርጎ ዲሮ፣ እድሜ 68፣ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ፣ (ቃለ መጠይቅ፣ ዳዋ ቡርሳ ቀበሌ፣ ጥቅምት 21 2006)፡፡

ዕድር መግባት አለመግባት ማኅበራዊና ስነልቦናዊ ጫና አለው። ዕድር በገባና ባልገባ ሰው የሚሰጠው አገልግሎት ይለያያል። ዕድር አለመግባት ለነገ አለማሰብ፣ ኃላፊነትን አለመወጣት፣ ራስን ከማህበረሰቡ እንደማግለል ይቆጠራል። ይህን በሚመለከት ለምሳሌ አቶ ወንድሙ ገብረየስ[8]"ገና ያልደረሰ ልጅ ካልሆነ በስተቀር ለአቅመ አዳም ደርሶ ያላገባ ቢሆንም እንኳን ዕድር ይኖረዋል።" ሲሉ የዕድር አባላትን የእድሜ ገደብ ጠቁመዋል። በዕድሮች ዝርዝር ውስጥ ያሉትን አባላት የእድሜ ገደብ ስንመለከት ትንሹ 19 ሲሆን ከፍተኛው 86 ነው። ስለዚህ ከወጣት እስከ አዛውንት የዕድር አባላት ናቸው።

ከላይ ከተጠቀሱት ሀሳቦች እንደምንረዳው ዕድር በዕድርተኛው ዘንድ እንደ ቤተሰብ እዳ ተሸካሚ ሆኖ የሚታይ፣ አለኝታ ተደርጎ የሚታመንበት፣ ሁሉንም የሚያገለግል፣ አድልዖ የሌለበት፣ ከዚህም በላይ ጉርብትናን መሠረት ያደረገ፣ ወዘተ፣ አብሮነትን፣ መረዳዳትን፣ በአጠቃላይ፣ የመቻቻል ባሕርያትን የሚገልፅ ተግባራዊ ተቋም መሆኑን ነው፡፡ በተጨማሪም ሰዎች ለዕድር ያላቸውን ከፍተኛ ግምት ብቻ ሳይሆን የኀልውና ጉዳይ አድርገው የሚመለከቱት መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ይህን ቁልፍ ከሆኑ መረጃ ሰጭዎች መካከል አቶ አህመተ-ዘማርያም[9]፡- "ዕድር የውዴታ ሳይሆን የግዴታ ነው። ምክንያቱም ሞት ለማንም የማይቀር ግን የማይለመድ ቀጠሮ የሌለው ዕዳ ነው፡፡ አንድ ሰው ሃይማኖቱን ለውጦ ካልተገለለ በስተቀር የኖረበትን ዕድር ትቶ መውጣት ቀርቶ አቅሙ እስከፈቀደለት ድረስ ከሶስት፣ ከአራት ዕድሮች ይገባል፡፡ ሞትን ያህል ዕዳ ተሸክሞ ያለ ዕድር ብንኖር ምን እንሆናለን?!" ብለው የሚያረጋግጥ ይሆናል፡፡ አንድ ሰው "ዕድር አለኝ" ሲል ከሚገኘው ቁሳዊ ድጋፍ በላይ "ጦሮ የሚቀብረኝ ልጅ አለኝ" የማለት ያህል በራሱ የስነልቦናዊ እርካታ የሚሰማው መሆኑንም ጨምሮ የሚያመለክት ነው።

ቀደም ሲል ዕድሮች በቃል በሚተላለፉ ተግባራትና ደንቦች ነበሩዋቸው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን ዓላማና ደንቦችን በፅሑፍ ማስፈር የተለመደ አሠራር እየሆነ ነው፡፡ የየዕድሮቹ መተዳደሪያ ደንቦችና ዓላማዎች ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ ቢሆንም በአደረጃጀት ወይም በአወቃቀርና በአባላት ብዛት አንዱ ከሌላው ይለያያሉ፡፡ ደንቦቹም ስለ ዕድርተኞች አባልነት መሥፈርቶች፣ የአባላት መብቶችና ግዴታዎች፣ ስለ ዕድር ዓይነቶች፣ ተግባርና አገልግሎት፣ ስለ መሪዎች ወይም ስለ አስተባባሪዎች በዝርዝር የሚገልፁ ሆነው ይገኛሉ። ረዘም ያለ እድሜ ካስቆጠሩ ዕድሮች መካከል "አንደኛ"፣ "ሁለተኛ" እና "ምሥራቃዊ ሦስተኛ ሸንኀ" ተብለው የሚታወቁት ዕድሮች ናቸው፡፡ እነዚህ ዕድሮች ከ65 ዓመታት በላይ የአካባቢው ማኅበረሰብ ያለማቋረጥ ሲገለገልባቸው የኖሩ ማኅበራዊ ተቋማት ናቸው፡፡

---

[8] መረጃ ሰጭ፡- አቶ ወንድሙ ገብረየስ፣ እድሜ 74፣ የኢ.ኦ ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታይ፣ ጡረተኛ፣ የሶስተኛ ምስራቃዊ ሸንኀ መስራች፡፡ ቃለ-መጠይቅ በበቆጂ ከተማ፣ ህዳር 7 ቀን፣ 2006፡፡

[9] መረጃ ሰጭ፡- አቶ አህመተ ዘማርያም፣ እድሜ 94፣ የባህል መድህኒት አዋቂ፣ የኢ.ኦ.ተ .ቤ ሃይማኖት ተከታይ (ቃለ መጠይቅ፣ በዲዳዋ ቀበሌ ጥር 15 2007)፡፡

ከእነዚህ ዕድሮች መካከል የመጀመሪያው ዕድር "አንደኛ ሸንጎ" - የበቆጂ ከተማ ከተቆረቆረች[10] ከአሥራ አምስት ዓመት በሁዋላ በ1941 ዓ.ም ገደማ በእስልምና እና በክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ትብብር ተቋቋመ፡፡ ዕድሩ ከከተማዋ መቆርቆር ጋር ተያይዞ የተመሠረተ ነው፡፡

ዕድር የሚተዋወቁ ሰዎች በፈቃደኝነት የሚመሠርቱት ባህላዊ-ማህበራዊ ተቋም በመሆኑ መሥራቾቹ ከመተዋወቅ አልፎ የጋራ ፍላጎት ያላቸው ናቸው፡፡ ፍላጎቱ የሚመጣው በመቀራረብና አንዱ ሌላውን በማክበር በመተሳሰብ አንዱ ለሌላው መኖር እውቅና በመስጠት የሚጠነከር ነው፡፡ ለምሳሌ ጥናቱ ካተኮረባቸው ዕድሮች መካከል በ1958 ዓ.ም የተጀመረውና ከሀምሳ አመት በላይ ያስቆጠረው "ሶስተኛ ዕድር" ከጀማሪዎቹ አንዱ የሆኑት አቶ ወንድሙ ገብረየስ11 ሲመልሱ፡-

> ሸንጎውን የመሠረትንበት ምክንያት አንድ ጓደኛችን ሲሞት ለቀብር የሚያስፈልጉ ነገሮችን መግዣ ገንዘብ ጠፋ። ከዚያ ጓደኞቹ ተሰባሰብንና አስር አስር ሳንቲም አዋጣን። በዚያም የሚያስፈልገውን ሁሉ ገዝተን ተቀበረ፡፡ እንግዳውም በጥሩ መስተንግዶ ተሸኘ። እዚያው ለቅሶ ቤት እንደ ተቀመጥን በጨዋታ መሀል ድንገት 'ለምን ለጓደኞችን ቀብር ያዋጣነውን አስር አስር ሳንቲም በየ15 ቀኑ አዋጥተን ሸንጎ አይሆንም?' የሚል ሀሳብ ተነሳ። ሁላችንም በዚሁ ሀሳብ ተስማምተን በሚያዝያ ወር 1958 ዓ.ም በየ15 ቀኑ መዋጮ 10 ሳንቲም እንዲሆን፣ ሊቀመንበር፣ ጸሀፊ፣ ገንዘብ ያዥ እቃ ግዢ መርጠን ዕድሩ ተጀመረ።

አቶ ወንድሙ ቀጥለው እንደሚያስረዱት በዚህ መልክ በአርባ አባላት የተመሠረተው ዕድር ዛሬ ከጀማሪዎቹ መካከል በህይወት የቀሩት ሶስት ብቻ ናቸው። አዳዲስ አባላት እየገቡ 198 አባላት ያሉት ትልቅ ዕድር ለመሆን እንደበቃ፣ የአመራር አባላቱ በሁለት ሳምንት አንዴ እሁድ እየተገናኙ አስፈላጊ የሆኑ እቃዎች እየገዙ እንደቀጠሉ፣ የወር መዋጮ ክፍያውም ከአስር ሳንቲም ወደ ሀያ አምስት ሳንቲም እያለ፣ በየጊዜው እየጨመረ ዛሬ አምስት ብር ደርሷል። በየሁለት ሳምንት አንዴ በተረኛ አባል ቤት ይደገስ የነበረው ቀርቶ የዕድሩ ንብረት በሆነው ቤት ውስጥ እንደሚሰበሰቡ ይተርካሉ፡፡

### 3.1 የዕድሮች ስያሜና አደረጃጀት

ዕድሮች በአባላት የመኖሪያ ሠፈር፣ በጾታና በሃይማኖት ላይ መሠረት አድርገው ይደራጃሉ ወይም ይዋቀራሉ፡፡ በፆታ 'የሴት ዕድር' እና 'የወንድ ዕድር' ተብለው ይደራጃሉ። 'የሰፈር ዕድር' እና 'ትልቁ ዕድር' በሚል ይለያሉ፡፡

በስያሜ ደረጃ በዕድሮች መካከል 'ትልቁ' እና 'ትንሹ ዕድር' በሚል ተለይተው ይጠቀሳሉ፡፡

---

[10] የበቆጂ ከተማ የተቆረቆረችው በ1929 ዓ.ም አካባቢ እንደሆነ ይገመታል፡፡ ለመመሥረቷ ምክንያት የሆነው የፋሽስት ኢጣልያን ወረራ ነበር (ፍሬህይወት፣ 2000፡ 13)። ይህም የሚያሳየው የበቆጂ ከተማ በተቆረቆረች በአስራ አምስተኛ ዓመቷ "አንደኛ ዕድር" የሚባለው የመጀመሪያው ዕድር መቋቋሙን ነው፡፡

[11] መረጃ ሰጭ፡- አቶ ወንድሙ ገብረየስ፣ እድሜ 74፣ የኢ.ኦ ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታይ፣ ጡረተኛ፣ (ቃለ-መጠይቅ በበቆጂ ከተማ፣ ህዳር 7 ቀን፣ 2006)፡፡

ለምሳሌ በበቆጂ ከተማ አስተዳደር ‘አንደኛው’ በሚል የሚጠቀሰው የመጀመሪያው ትልቁ ዕድር ነው፡፡ ይህ ዕድር በበቆጂ ከተማ ውስጥ አንጋፋውና ከተቋዋቁዋሙት ሁሉ በምሳሌነት የሚጠቀስ፣ ከተመሠረተበት ከ1941ዓ.ም አንስቶ ያለማቋረጥ የቀጠለና የረዥም ጊዜ ልምድ ያካበተ ነው፡፡ አብዛኞቹ ዕድሮች የመተዳደሪያ ደንባቸውን ያዘጋጁት ከዚሁ ከትልቁ ዕድር ላይ ተመሥርተው ነው፡፡ ‘አንደኛው ትልቁ የወንዶች ዕድር’ የሚለውን መጠሪያ ስም ያሰጠውም ይኸው ለሌሎች ከእሱ ቀጥለው ለተመሠረቱት ዕድሮች ግንባር ቀደም መሆኑ ነው፡፡ የዚህ የአንደኛው ትልቁ የወንዶች ዕድር አባላት አብዛኞቹ ወንዶች ሲሆኑ ጥቂት የሴት አባላትም አሉት፡፡ የሴት አባላቱ በዚህ የትልቁ የወንዶች ዕድር አባል ለመሆን የቻሉት ባሎቻቸው የሞተባቸው መበለቶች፣ ከባላቸው የተፋቱና ባሎቻቸው በተለያየ ምክንያት አካባቢውን ለቀው የሄዱባቸው ሴቶች ናቸው። ባል እያለ ግን ሚስት የትልቁ የወንዶች ዕድር አባል የሆነችበት ኢጋጣሚ እስካሁን እንደሌለ ጠቁመዋል። ይህም ሳይወያዩ ከተስማሙባቸው ደንቦች ውስጥ አንዱ ነው። የዕድሩ አባል የሆነ ባል፣ እርሱ በሌለበት ወቅት ሚስቱ እርሱን ተክታ በቦታው አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮችን በሙሉ መፈጸም ትችላለች። ብዙዎቹ በሁለት ሳምንት አንድ ቀን ጠዋት፣ ጥቂቶቹ ደግሞ ወር በገባ የመጀመሪያው እሁድ ለቋሚ መዋጮ እንዲሁም የሚወያዩበት ርእሰ ጉዳይ ካላቸው ለመወያየት ይገናኛሉ።

በበቆጂ ከተማ ከአንደኛው ትልቁ የወንዶች ዕድር ቀጥለው የተደራጁ ዕድሮች እንደ አመሠራረታቸው ቅደም ተከተል ‘ሁለተኛው ትልቁ’፣ ‘ሦስተኛው ትልቁ’፣ … እየተባሉ በቁጥር እየተቆጠሩ ቀጥለዋል፡፡ ይህም በቁጥር አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ፣ … ተብለው የተሠየሙበት ምክንያት ዕድሮቹ የተመሠረቱበትን የዘመን ቅደም ተከተል የሚያስታውስ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- አንደኛው ከላይ እንደተጠቀሰው በ1941 ዓ.ም፣ ሁለተኛው በ1955 ዓ.ም፣ ሶስተኛው በ1958 ዓ.ም.፣ አሥራ ስምንተኛው በ2003 ዓ.ም የተቋቋሙ ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ በቁጥር መጠራታቸው እንዳለ ሆኖ ተጨማሪ ስም አላቸው። ለምሳሌ፣ የጥምቀተ-ባህር ስምንተኛ ሸንጎ፣ አስረኛ የአንድነት ሸንጎ፣ ወዘተ፣ ይባላሉ። የአንዳንዶች ስም በአባላቱ የሥራ መስክ ወይም ሙያ፣ በመኖሪያ አካባቢ ስም እንዲሁም በመሰባሰቢያ ሠፈራቸው ስም፣ ወዘተ፣ ይታወቃሉ፡፡

በሥራ መስክ ወይም በሙያ የተራደጁ ዕድሮችን በሚመለከት መሥራች ከሆኑት አንዱ አቶ ወንድሙ ገብረየስ[12] እንደሚከተለው ትውስታቸውን ይገልፁታል-

> ከዕድራችን ውጭ ያሉ ሌሎች ሰዎች ‘የኩሊዎች’ ዕድር ብለው ለእድራችን ስም ሰጡን። የዕድሩ አባላት የእስልምናና የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታዮች በዘርም ቢሆን የማንመሳሰል ብንሆንም ሙያችን ውሏችን ያስተሳሰረን ነበር። የምንሰራውም አናጺነት፣ ግንበኝነት፣ የተገኘውን የቀን ሥራ ነበር። ተሰባስበን ዕድር መሠረትን በኋላ ከእኛ በፊት የነበሩት ዕድሮች ባላባቶችና የባላባት ልጆች እንዲሁም የጠገቡ ነጋዴዎች ነበሩ፡፡ እኛንም ድህነታችንን ሊነግሩን ‘የኩሊዎች ዕድር’ ብለው ስም ሰጡን፡፡ በኋላ ደግሞ ዕድራችን እየሰፋ

[12] መረጃ ሰጭ፡- አቶ ወንድሙ ገብረየስ፣ እድሜ 74፣ የኢ.ኦ ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታይ፣ ጡረተኛ፣ የሶስተኛ ምስራቃዊ ሸንጎ መስራች፡፡ ቃለ-መጠይቅ በበቆጂ ከተማ፣ ህዳር 7 ቀን፣ 2006፡፡

> ትምህርት ቤት በከተማ ውስጥ ተከፍቶ ብዙ መምህራን እኛ ዕድር ገቡ፡፡ መምህራን የእድራችን አባል ሲሆኑ ሊቀመንበር ፀሀፊ ገንዘብ ያዥ የቀድሞዎቹን አውርደን መምህራኑን አደረግን፡፡ ይህን ሲያዩ ደግሞ የመምህራን ዕድር ብለው ኩሊዎች የሚለውን ቀየሩት፡፡ ከዚያ አንድ ቀን ተሰባስበን እንዳለን ነፍሱን ይማረው አንድ ጓደኛችን "እኛ ባለቤቶቹ እያለን ሌላ ሰው ለእኛ ዕድር ለምን ሥም ያወጣልናል? እኛ ለምን ለራሳችን ሥም አናወጣም?" ብሎ ሀሳብ አቀረበ፡፡ ተወያየን፤ ብዙ አማራጭ ቀረበ፤ ተከራከረን ተከራከረን በኋላ 'ምሥራቃዊ ዕድር' በሚለው ተስማማን፡፡ 'ምሥራቃዊ' የሚለውን ስም የሰጠንበት ምክንያት በዚያን ጊዜ ዕድሩን የመሰረትነው መኖሪያ ቤታችን በከተማው ዳር ላይ በስተምሥራቅ ስለነበረ ነው።

በሙያ ተመሳሳይነት ያላቸው ዕድሮችን የመሰረቱትን ዕድርተኞች ከቡድኑ ውጭ ያሉ ሌሎች ቡድኖች ማንነት ለመጠቆም "የኩሊዎች ዕድር" ብለው ይጠሩት ነበር፡፡ ይህም የሚያሳየው ሌላው ቡድን የሰጣቸው ስም ከመጠሪያነት ባሻገር በዘመኑ ለሙያው ይሰጠው የነበረውን ዝቅተኛ ግምት ወይም ቦታ ያንፀባርቃል፡፡ ቀድሞ ከተመሠረተው ከአንደኛና ከሁለተኛው ዕድር ጋር ሶስተኛው ዕድር ሲነጻጸር የሁለቱ ዕድሮች በኢኮኖሚ ደረጃቸውና በማህበራዊ ደረጃ በመጀመሪያው ተርታ የሚቀመጥና እራሳቸውን በሶስተኛው ዕድር ካሉት ከፍ አድርገው የሚመለከቱ ነበሩ፡፡ ዛሬ "የኩሊዎች ዕድር" ይባል በነበረው ዕድር ውስጥ የሚገኙት አባላት እንደ አጀማመሩ የቀን ሠራተኞችንና መምህራንን ብቻ የያዘ ሳይሆን የተለያየ ሙያና የተለያየ ማህበራዊ ዳራ ያላቸውን አባላት ያካተተ ሆኗል፡፡

የአባላትን መኖሪያ መሠረት በማድረግ "የሰፈር ዕድር" ይቋቋማል፡፡ ስሙ እንደሚያመለክተው የሰፈር ዕድር በአንድ መንደር ወይም አካባቢ በጉርብትና የሚኖሩ ሰዎች ተሰባስበው የሚመሠርቱት ነው። በአብዛኛው ከመንገድ በላይና በታች፣ አለያም በቦታ የሚቋቋም የዕድር ዓይነት ነው። ከትልቁ የወንዶች ዕድር የሚለየው በሚሰጡት አገልግሎትና አባላቱ በአንድ አካባቢ ብቻ በጉርብትና የሚኖሩ መሆናቸው ነው። "ሁሉም የሰፈር ዕድር አባላት የትልቁ ዕድር አባላት ናቸው። ለምሳሌ እኔ ከሶስተኛ ዕድር በተጨማሪ የሰፈር የወንዶች ዕድር አባል ነኝ።" የትልቁን ዕድር አገልግሎት ታሳቢ በማድረግ ለመሸፈን የማይችሉ ነገሮችን ለማካካስ የተቋቋመ በመሆኑ የሰፈር ዕድር በትልቁ ዕድር ላይ እንደ ተጨማሪ ሆኖ የሚሠራ ነው።[13] የሰፈር ዕድር፣ ትልቁ ዕድር አገልግሎት በማይሰጥባቸው ጊዜ ሀዘን ለደረሰባቸው አባላት የትልቁን ዕድር ያህል ብዙ ባይሆንም የተለያዩ ቁሳቁሶችን በማዋስና መጠነኛ የገንዘብ ድጎማ በመስጠት በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት አስተዋጽኦ ያደርጋል።

በሰፈር ዕድሮች አወቃቀር ፆታን በሚመለከት በልምድ ዳብሮ የቆየና ዛሬም የሚተገበር የአደረጃጀት አሠራር አለ። ለመገንዘብ እንደተቻለው የዚህ አገልግሎት መሠረታዊ መርህ "በባህሉ በልማድ በሴቶች እና የወንዶች የሥራ ክፍፍል ላይ መሠረት ያደረገ ነው።" የእድሩ አባላትም ሆኑ ወንዶቹ "የሴቶች ዕድር" ከማለት ይልቅ "የሴቶች ባልትና" ብለው መጥራትን

---

[13] መረጃ ሰጭ፡- መምሬ ለገሰ ጎሳ፣ እድሜ 82፣ የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታይ፣ የባህል መድኅኒት አዋቂ፣ (ቃለ-መጠይቅ በቆጂ ከተማ 02 ቀበሌ ህዳር 19 ቀን፣ 2006)፡፡

ያዘወትራሉ። መተዳደሪያ ደንባቸውም በጽሁፍ ሰፍሮ የሚገኘውም የሴቶች ባልትና ተብሎ የየራሱ መጠሪያ ይኖረዋል። ለምሳሌ "የኪዳነምህረት የሴቶች ባልትና" አንዱ ነው። 'ባልትና' የሚለው ሥም የተሰጠበት ምክንያት ዕድርተኞቹ በለቅሶ ቤት ከሚሰጡት ሙያዊ አገልግሎት የተነሳ ነው። እነዚህ ዕድሮችም 'ትልቁ የሴቶች' እና 'የሰፈር የሴቶች ዕድር' የሚል ሁለት ዓይነት መደብ አላቸው፡፡ የሴቶች ዕድር አባላት ሙሉ በሙሉ ሴቶች ናቸው። በእርግጥ ወንዶች ወደ ሴቶች፣ ሴቶች ወደ ወንዶች ዕድር እንዳይገቡ የሚከለክል ደንብ የለም። ነገር ግን በሁለት የሴቶች ዕድር አንዳንድ አባላት ወንዶች የነበሩበት በዚህ ጥናት ተዳሰው ነበር። ወንዶቹ እንዴት አባል እንደሆኑ ሲጠየቁ ሚስቶቻቸው አርፈው በምትካቸው እንደገቡና የዕድሩ አባላት በሚሰሩት ምግብ ማብሰል ተግባር ላይ እንደማይሳተፉ ተሳትፏቸው በመስተንግዶ ብቻ እንደሆነም ገልጸዋል። ትልቁ የሴቶች ዕድር ከሰፈር ዕድር የሚለየው በከተማ ክልል ውስጥ የሚገኙ መተዳደሪያ ደንቡ ያስቀመጣቸውን መስፈርቶች የሚያሟሉ ሴቶች ሁሉ አባል መሆን መቻላቸው ነው፡፡ የመጀመሪያው ትልቁ የሴቶች ዕድር በቆጂ ከተማ በ1949 ዓ.ም አካባቢ እንደ ተመሠረተና ብዙ ቆይቶ መፍረሱን መረጃ ሰጭዎች ይጠቁማሉ፡፡[14] ሁለተኛው የሴቶች ባልትና የተቋቋመው በ1955 ዓ.ም ነበር። ይህ ዕድር እስከ አሁን እንደቀጠለ ይገኛል፡፡

የመጀመሪያው የሴቶች ዕድር ከተቋቋመ በኋላ ሌሎች መሰል ዕድሮች እየተስፋፉ ሄደዋል። ዛሬ "ከሰላሳ በላይ የሴት ዕድሮች በከተማ ውስጥ እንዳሉ ይገመታል፡፡"[15] የሴት ዕድሮች በዓላትን[16] አስታከው በወር አንድ ቀን በተረኛዋ ቤት ምግብና መጠጥ ተዘጋጅቶ ይገናኛሉ። ለምሳሌ የኪዳነ-ምህረት ዕድር መተዳደሪያ ደንብ (1998 ገጽ የሌለው) ዘወትር መደበኛ ሆነው ከሚሠፍሩት ደንቦች በተጨማሪ፡-

> አንዲት አባል መሆን የፈለገች ሴት 'ዕድራችሁ ልግባ' በማለት ከነባር አባላት ለአንዷ መልእክት በመላክ ትጠይቃለች። ነዋሪ ከሆነች 'ለምን እስካሁን ዕድር አልኖራትም ብለን እንጠይቃለን።' እሷም የሚያሳምን ምክንያት ከነገረችን ይፈቀዳል። ካልሆነ ግን አንፈቅድም። ምክንያቱም ከሌላ ዕድር በጠባያቸው አስቸግረው ተባረው የሚመጡ ሴቶች ስላሉ እነሱን አናስገባም። ገና ትዳር የያዘች ወይም ከሌላ ሀገር ተቀይራ የመጣች ከሆነችና በፅሁፍ ያለውን መስፈርት ካሟላች እናስገባታለን።[17]

በቅርብ ዘመድ ላይ የሞት አደጋ ሲደርስ አባላቱ በምን መልኩ እንደሚረዳዱ ደንቡ በዝርዝር አስፍሯል። ለምሳሌ፡-በቀብሩ ዕለት ከንጋቱ ከአሥራ ሁለት ሰዓት በፊት ወደ ለቅሶው ቤት

---

[14] መረጃ ሰጭ፡- ወ/ሮ ሙሽሪት ሲራጅ፣ እድሜ 48፣ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ፣ በንግድ ስራ የሚተዳደሩ፡፡ ቃለ-መጠይቅ በበቆጂ ከተማ፣ ጥር 19 ቀን፣ 2007፡፡

[15] መረጃ ሰጭ፡- ወ/ሮ የሺ ግርማ፣ እድሜ 59፣ የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታይ፣ ጡረተኛ፡፡ ቃለ-መጠይቅ በበቆጂ ከተማ፣ ህዳር 11 ቀን፣ 2006፡፡

[16] ለምሳሌ በ5 የአቦ ሸንጎ፣ በ7 የስላሴ፣ በ12 የሚካኤል፣ በ13 የእግዚአብሄር አብ፣ በ16 የኪዳነምህረት እያለ ይሄዳል። እነዚህ ስሞች የዕድሩ መጠሪያ ሲሆኑ ዕለቱ ደግሞ ወርሀዊ መገናኛ በመሆን ያገለግላል። አንዳንዶቹ በተመሳሳይ ስምና ቀን የሚጠሩ አሉ። ይህን ቀን ለመምረጥ ከበአሉ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም።

[17] የመረጃ ምንጭ፡- ወ/ሮ መዓዛ ወንድሙ፣ እድሜ 49፣ የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታይ፣ የአቦ የሴቶች ዕድር ዳኛ(በቆጂ ከተማ 01 ቀበሌ ጥር 24/2007)፡፡

በመድረስ ለእንግዳ መሸኛ የሚሆን ምግብ፡- ንፍሮ በመቀቀል፣ እንጀራ በመጋገር፣ ወጥ በመሥራት፣ ሻይ በማፍላት፣ ወዘተ፣ በማዘጋጀት ይተባበራሉ።[18] ከዚህ በተጨማሪ አባላቱ አምስት፣ አምስት እንጀራ እና ሁለት፣ ሁለት ብር በማዋጣት ለቡና ማፍያ የማድረስ ግዴታ አለባቸው። የሴቶችን ዕድር አገልግሎት በተመለከተ ልዩ የሚያደርገው አንደኛው ደንብ "ሬሳ ካለበት ቤት አባላቱ የህብረት ሥራ ይሰራሉ፤ ግማሽ አባል ...ለሶስት ተከታታይ ቀናት ሁለት ሴቶች ተመድበው እንዲያድሩ" መደረጉ ነው (የገብርኤል የሴቶች ባልትና መተዳደሪያ ደንብ፣ 1989፣ ገጽ የሌለው)፡፡

በአጠቃላይ የወንድ፣ የሴት፣ የሰፈር፣ ትልቁ የከተማ የገጠር የሚሉ የዕድር ዓይነቶች ዋና ትኩረት አንድ ሰው ሲሞት አስክሬኑን በክብር መሸኘት፤ ሀዘንተኞችን ማጽናናት፣ በጉልበትና በገንዘብ መርዳት፣ ለለቀስተኛ እንግዶች ምግብ ማዘጋጀትና ማስተናገድ ነው። እያንዳንዱ ዕድር በፅሁፍ የሰፈረ መተዳደሪያ ደንብ አለው፡፡ ደንቡን ሲያወጣም አባላቱ በረቂቁ ላይ ተወያይተው፣ የሚጨመረውን ጨምረው፣ የሚሻሻለውን አሻሽለው፣ መተዳደሪያ ደንብ አድርገው ማጽደቃቸውን ሁሉም በፊርማቸው ያረጋግጣሉ። ውስጠ ደንቦቹ የሚያተኩሩባቸው ጉዳዮችም፡ - ስለ የጠቅላላ ጉባኤ ስልጣን፣ ማህበሩን ስለሚመሩ የተለያዩ ኮሚቴዎች ሀላፊነትና ተግባር፣ ስለ አባላት መብትና ግዴታ እንዲሁም ስለ ማህበሩ የገቢ ምንጭ፣ ወዘተ፣ ናቸው። አወቃቀራቸውም ሊቀመንበር፣ ጸሀፊ፣ ገንዘብ ያዥ፣ ንብረት ክፍል፣ ሂሳብ ሹም፣ ጥሩንባ ነፊ፣ ወዘተ፣ ያጠቃልላል (አስራ አንደኛው ሸንጎ፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ 1996፡ 1-8)። በደንቦቹ የተጠቀሱት አንቀፆች እንደሚገልፁት የእርዳታ አሰጣጡ በዝምድና ቅርበት ልዩነት አለው። ትልቁ እገዛ የእድሩ አባል ወይም ባለቤቱ፣ ቀጥሎ ልጅ፣ ከዚያ እናት አባት፣ እህት ወንድም እንዲሁም ደራሽ እንግዳ እያለ መጠኑ ያንሳል።

### 3.2 የአባልነት መሥፈርቶች

አንደኛው መስፈርት፤ የመኖሪያ አካባቢ ቅርበትና ርቀትን የሚመለከት መስፈርት ነው። ለምሳሌ፡- ትልቁ የወንዶችም ሆነ የሴቶች ዕድር የከተማ ክልልን ብቻ የሚያካትት መሆኑን ይገልጣል፡፡ ወደ ዕድር ለመግባት ለጠየቀ ግለሰብ ደንቡ ይነገረዋል እንጂ የመኖሪያ አካባቢውን የሚያመለክት ማረጋገጫ እንዲያቀርብ አይገደድም፡፡ ሆኖም ግን በገጠር ቀበሌ ገበሬ ማህበራት ነዋሪ ሆኖ ሳለ "የበቆጂ ከተማ ክልል ነዋሪ ነኝ" ብሎ ወይም ከገጠር መጥቶ በከተማ ባሉ ዕድሮች ውስጥ ካልገባሁ የሚል ከሆነ በገደብ ይገባል። ገደቡም የገንዘብ እገዛ ከማድረግ ውጭ አባላቱ በጉልበት አያግዙትም። ይህንን ደንብ ስድስተኛው ዕድር እንደሚከተለው በጽሁፍ አስፍሮታል፡፡ "የዕድር አባል ለመሆን የሚችለው በበቆጂ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ነዋሪ የሆነ ግለሰብ ነው።

[18] ለአገልግሎት ከሚውሉት እቃዎች መካከል ብረት ድስት፣ መክተፊያ፣ ቢላ፣ ወጥ ማውጫ እግራም ሰሀን፣ ጭልፋ፣ እቃ ማጠቢያና ማድረቂያ፣ የሻይና የውሃ መጠጫ ኩባያ፣ ሰፌድ ይገኙበታል። እነዚህ እስከ ተወሰነ ቀን ድረስ በውሰት በሀዘንተኛዋ ቤት የሚቆዩ መገልገያ ቁሳቁሶች ናቸው። ለምግብ ዝግጅት ግብዓት ከሚሆኑት ለምሳሌ ሽሮ፣ በርበሬ፣ የምስርና የአተር ክክ የመሳሰሉትን የሚያቀርቡ ሲሆን አሰጣጡም እንደየ ዕድሩ ደንብ ይለያያል። ለምሳሌ የአቦ ዕድር ሬሳ ለወጣበት ለቅሶ ቤት ሶስት ጆግ በርበሬ፣ ስድስት ጆግ ሽሮ፣ እንዲሁም ለዘይት መግዣ ሁለት መቶ ብር፣ መርዶ ከሆነ ሁለት ጆግ በርበሬ፣ ሶስት ጆግ ሽሮ ለዘይት መግዣ 100 ብር ይሰጣል(የኪዳነምህት ዕድር 1998፡ ገጽ የሌለው)።

ከከተማው ክልል ውጭ በገጠር ቀበሌዎች የሚኖር የዕድር አባል ከማህበሩ የሚያገኘው አገልግሎት የገንዘብ ድጋፍ ብቻ ይሆናል። የማቴርያልና የአባላት የጉልበት ድጋፍ አይደረግለትም" (ስድስተኛ ሸንጎ መተዳደሪያ ደንብ 2001፡ 7)። የመሥፈርቱ ዓላማ በሀዘን ጊዜ ለመረዳዳት ርቀት መንገድ ላለመጓዝ እና ትብብሩን ውጣ ውረድነት ለመቀነስ የታሰበ ይመስላል።

ሁለተኛው መስፈርት፤ አንድ አዲስ አባል ወደነባር ዕድር ለመግባት ሲፈልግ በዕድሩ ውስጥ የተደራጁ የቅርብ ዘመዶች የሌሉት መሆኑን የሚመለከት ነው። ይህ ደንብ የዕድሩ የገንዘብ አቅም እንዳይጎዳ ለመከላከል የወጣ ነው፡፡ ጉዳቱም ለምሳሌ በጥሬ ገንዘብ ሲታይ የአንድ ዕድር አባል የሆኑ አራት እህትማማቾች ቢኖሩ እናት ወይም አባት ቢሞታቸው ዕድሩ ከሚጠበቅበት ግዴታ መካከል አንዱ አንድ እናት የሞተበት(የሞተባት)የዕድር አባል ጥሬ ገንዘብ መስጠት ነው። በመሆኑም ለአራት ግለሰቦች በአንዴ ገንዘብ መስጠት ለዕድሩ አባላት ጫና ይኖረዋል ከሚል የመነጨ ነው።

ሶስተኛው መስፈርት፤ የቅድሚያ ክፍያ የመፈፀም የሚጠይቅ ነው፡፡ ክፍያው ከዕድር ዕድር ሊለያይ ይችላል፡፡ ለምሳሌ ለሁለተኛው ዕድር ለአባልነት የሚያበቃው ትልቁ የክፍያ መጠን 2000 (ሁለት ሺህ) ብር ሲሆን ዝቅተኛው ደግሞ 300 (ሶስት መቶ) ብር ነው። ይህን የተወሰነውን የገንዘብ መጠን በአንድ ጊዜ መክፈል ያልቻለ ግለሰብ እስከ ስድስት ወር ባለው ጊዜ ከፍሎ ማጠናቀቅ ይፈቀድለታል።

አራተኛውና ከዚህ ጥናት ትኩረት አንዱ የሆነው መስፈርት ለዕድር የአባልነት ጥያቄ ያቀረበው ግለሰብ ሃይማኖታዊ ማንነትን የሚጠይቀው መሥፈርት ነው፡፡ በነባር እና አዲስ በተመሠረቱ የተለያዩ ዕድሮች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን እና/ወይም የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ መሆንን የሚያበረታቱ ወይም የግድ የሚጠይቁ ሆነው ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ በበቆጂ ከተማ የሁለተኛ ዕድር የመተዳደሪያ ውስጠ ደንብ፡-

> የማህበሩ አባል መሆን የሚችለው የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ ወይም የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ መሆን አለበት።...ከሁለቱ እምነቶች ውጪ የሚከተል ወደ ዕድሩ መግባት አይፈቀድለትም። ነባር አባል የነበረበትን ሃይማኖት መቀየር ካስፈለገው ዕድሩን በፈቃዱ እንደለቀቀ ተቆጥሮ ከዕድሩ ይሰረዛል" (2002 አንቀፅ 4፤ 2)።

መረጃዎች እንደሚያሳዩት በዕድሮች ሕገ-ደንቦች ውስጥ ይህ መመዘኛ በተለይም ከ1982 ዓ.ም በፊት አልነበረም፡፡ ከ1982ዓ.ም ወዲህ ግን መመዘኛውን ለማውጣት "አስገዳጅ ምክንያት የሆነው የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ወደ አካባቢው መምጣት ነው፡፡ ቀድሞ ያልነበረው ሃይማኖት በአካባቢው እየተስፋፋ መምጣት መስፈርቱን ለመጠቀም ግድ አድርጎታል።"

አንድ ግለሰብ የዕድሩ አባል መሆን ስለፈለገ ብቻ የእስልምና ወይም የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታይ ሳይሆን "ነኝ" ብሎ ዋሽቶ ቢመዘገብና እውነተኛ ሃይማኖቱ ታውቆ ከዕድሩ ሳይባረር

ቀርቶ የቅርብ ዘመድ ቢሞትበት ከዕድሩ ምንም ዓይነት አገልግሎት አያገኝም። ምክንያቱም በሃይማኖት ልዩነት የቀብሩ ቦታ ስለሚታወቅ እንዲሁም የህዝቡ ቁጥር አነስተኛ መሆንና እንግዳ ሰው ስለማይበዛ እርስ በእርስ ለመተዋወቅ አያዳግትም። አንድ የዕድር አባል የቅርብ ዘመዶቹ ሲሞቱ በተለያየ መንገድ መረዳት መብቱ ነው፡፡ ሆኖም ሟቾቹ የእስልምና ወይም የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታዮች መሆን አለባቸው፡፡

የእነዚህ ደንቦች በዕድር ውስጥ መካተት ዋንኛ ምክንያት የፕሮቴስታንት ሃይማኖት በአካባቢው እንዳይስፋፋ ለመግታት ሲባል ነው፡፡ መጋቢ ብሩክ[19] እንደሚሉት

> ይህ የታሰበውን ያህል ባይሆንም "ከዕድሬ ከምባረር ሃይማኖቴ ይቅርብኝ ያሉ ብዙ ግለሰቦች ነበሩ። ሰዎችን አሳምነን ወደ ሃይማኖቱ[ወደ ፕሮቴስታንት ሃይማኖት] ሊገቡ ከተስማሙ በኋላ በተለይ በእድሜ ገፋ ያሉት ከዕድር መባረራቸው ያሳስባቸው ስለነበር 'ቀባሪ አጣለሁ' የሚለው ስጋት አይሎ በዕድር ምክንያት ብቻ የቀሩ ብዙ ናቸው፡፡ ዛሬም ቢሆን ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን ያለውን ማህበራዊ ኑሮ እዚህ እኛ ዘንድ[የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታዮች] ስለማያገኙ ለአመታት ቆይተው ተመልሰው ወደ ቀድሞ ሃይማኖታቸው [ወደ ኢ.ኦ.ተ.ቤ]የተመለሱ ግለሰቦች ጥቂት የሚባሉ አይደሉም፡፡

በማለት ያስረዳሉ፡፡

### 3.3 የአለመቻቻል ምልክቶች፡- በፕሮቴስታንት እና በሙስሊም/በኢ.ኦ.ተ.ቤ

በዕድሮቹ የአባልነት መሥፈርቶች በግልጽ ሠፍረው እንደሚታየው፣ በአንድ በኩል በሙስሊምና በኢ.ኦ.ተ.ቤ አማኝ ማህበረሰቦች መካከል የሰመረ የመቻቻል ትስስር መኖሩን፣ በሌላ በኩል ደግሞ በእነዚህ በሁለቱ ሃይማኖታዊ ማህበረሰቦች እና በፕሮቴስታንት አማንያን መካከል አለመቻቻልን የሚያመለክቱ አዝማሚያዎችና ድርጊቶች መኖራቸውን እንገነዘባለን፡፡ በመሆኑም "ለዚህ እንደ ምክንያት ሆነው የሚቀርቡት ጉዳዮች ምንድን ናቸው?" ብለን እንድንጠይቅ ይገፋፋናል፡፡

መረጃ ሰጭዎች እንደሚገልፁት አንደኛው የልዩነቱ ዋነኛ ምክንያት የፕሮቴስታንት በተለይም የሙሉ ወንጌል ሃይማኖት በአካባቢው በይፋ ስብከት መጀመሩንና መስፋፋቱን አለመፈለግ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የልዩነቱ መንስኤ በአካባቢው ለረዥም ጊዜ ከቆዩት ሃይማኖቶች ውጭ ሌላ እንግዳ ወይም መጤ ሃይማኖት መከሰቱ ነው፡፡ ከዚህ የተነሳም "የፕሮቴስታንት

[19] ምንጭ፡- መጋቢ ብሩክ አለሙ፣ እድሜ 46፣ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታይ፣ የሌሙና ቢልቢሎ ሙሉ ወንጌል ቁጥር አንድ ቤተ-ክርስትያን አስተዳዳሪ፣ እንዲሁም የወረዳው የፕሮቴስታንት ሃይማኖት አስተዳዳሪ(ቃለ-መጠይቅ ሰኔ 19/2007)፡፡

ሃይማኖት ተከታዮችን ወደ ዕድራችን አትገቡም ነባሮቹም የእስልምና ወይም የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን ሃይማኖት ተከታዮች የነበራችሁ ፕሮቴስታንት ከሆናችሁ ከዕድሩ ውጡ መባል ተጀመረና በነባሮቹ ሃይማኖቶች እና በአዲስ ገቢው የፕሮቴስታንት ዕምነት መካከል ጉልኅ የአመለካከት ልዩነት ተከሠተ፡፡”[20] ቀጥለው እንደሚያስረዱት ማህበረሰቡም እነዚህን ሁለት ሃይማኖቶች ልዩነቱን በአንድነት ተቀብሎ ከፊሉ ሙስሊም ከፊሉ የኢ.ኦ.ተ.ቤ በማንኛውም ማኅበራዊ ግንኙነት ሳይነጣጠሉ አንድነት መስርተው ኑሯቸውን ከሚመሩበት መካከል አንዱ የሆነውን ዕድር አዲስ መጥ የሆነው የፕሮቴስታንት ሃይማኖት አብሮነቱን ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ አድርጎታል፡፡

ሁለተኛው ምክንያት የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታዮች ዕድርን እንደ ስብከት አጋጣሚ አድርገው የመጠቀም ጠባይና ድርጊት መሆኑን መጋቢ ብሩክ ጨምረው ያስረዳሉ፡፡ የዕድር ዓላማ የሃይማኖት ስብከት አይደለም፡፡ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታዮች ግን በየዕድሩ ተከታይ ለማብዛት ሰዎች ተሰባስበው የሚገኙበት አጋጣሚ ስለሆነ ብቸኛው የመስበኪያ አማራጭና ዘዴ አደረጉት፡፡ ቀድሞ ሙስሊም ወይም የኦርቶዶክ ሃይማኖት ተከታይ የነበሩት ሃይማኖታቸውን አስትተው የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታይ እንዲሆኑ መስበኪያ መሣሪያ አደረጉት ይህ ከዕድር አደረጃጀት ጋር በተያያዘ በአካባቢው ማህበረሰብ ቁጣ ቀሰቀሰ፡፡

ቀድሞ በዕድሮች መተዳደሪ ደንብ ውስጥ ያልነበረ የአባላትን ሃይማኖት የሚጠይቅ ደንብ እንዲወጣ አስገደደ፡፡ በመሆኑም የፕሮቴስታንት ሃይማኖትን ሃይማኖቴ ያሉ ግለሰቦች ወደ ዕድሮች እንዳይገቡ፤ ነባር አባላትም ወደ አዲሱ ሃይማኖት ከገቡ ከዕድር እንዲባረሩ በጽሁፍ በሰፈረው ደንብ ውስጥ ተካተተ፡፡ ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ የዕድር አባል ለመሆን የግለሰቡ ሃይማኖት አንድ መስፈርት ሆነ፡፡ ለምሳሌ፡-

> አንድ የዕድር አባል የእስልምና ወይም የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ ነኝ ብሎ ማንም ሳያስገድደው በፈቃዱ ወዶ ከፈረመ በኋላ የሌላ ሃይማኖት ተከታይ ሆኖ ከተገኘ ከዕድሩ መተዳደሪያ ደንብ ውጭ ስለሆነ በራሳቸው ፈቃድ የዕድሩን ደንብ ያፈረሱ በመሆኑ ጉዳዩ ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ቀርቦ ከተጣራ በኋላ ለጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ በውይይት በማጸደቅ ከአባልነቱ ይሰረዛል። ምክንያቱም ዕድሩ የተመሠረተበት አላማ የእስልምና ሃይማኖትና

[20] መረጃ ሰጭ፡- መጋቢ ብሩክ አለሙ፣ እድሜ 46፣ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታይ፣ የሌሙና ቢልቢሎ ሙሉ ወንጌል ቁጥር አንድ ቤተ-ክርስትያን አስተዳዳሪ፣ እንዲሁም የወረዳው የፕሮቴስታንት ሃይማኖት አስተዳዳሪ(ቃለ-መጠይቅ በቆጂ 02 ቀበሌ፣ ሰኔ 19/2007)፡፡

> የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ አባላት በአንድነት በመሰብሰብ የጋራ ችግራቸውን እንዲሁም ገንዘባቸውንና ጉልበታቸውን በማቀናጀትና በማስተባበር አንድም ጥላቻና እንቅፋት ሳይኖር የሌላ ሃይማኖት ጣልቃ ገብነት ሳይኖርባቸው፣ በዓለምም ሆነ በመከራ ለመረዳዳት ብቻ ሳይሆን ለሀዘንተኛው የአለንልህ ባይነትና ሀዘኑን በሚረሳባቸው የእህትማማችነትና የወንድማማችነት ድጋፍ እንዲያገኝ ለማድረግ ነው (አንደኛ ዕድር 2003፡25)።

የእድሩን አጀማመር በአካባቢው ነዋሪ ከነበሩት ነዋሪዎች የሃይማኖተ ዳራ አኳያ የዕድር መስራች ከሆኑት አንዱ እና ሌሎችም በወቅቱ የነበሩ ግለሰቦች በቡድን ውይይት የተገኘው ሀሳብ በአጭሩ የሚከተለው ነው።

ዕድር ስንመሠርት የኦርቶዶክስ እና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ነበርን። በዚያን ጊዜ በአካባቢው ከሁለቱ ሃይማኖት ተከታዮች ውጭ የሆነ ነዋሪ አልነበረም። በደርግ ጊዜ ግን ጥቂት "ሚሺኖች" በከተማ ውስጥ ነዋሪ ቢሆኑም ዕድር ግን አልነበራቸውም። ምክንያቱ ደግሞ በደርግ ሥርዓት "ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር" የሚል አዋጅ ታውጆ ነበር። እነዚህ ሚሺኖችም ወደ ጦርነት እንዲሄዱ ከተመለመሉት መካከል ቢኖሩበትም 'እኛ ሰው አንገድልም፤ ስለዚህ ጦርነት አንሄድም' አሉ። በዚህ ምክንያት ደርግ አብዮታዊ እርምጃ ወሰደባቸው። የቀሩትም ይደበቁ ስለነበር ዕድር አይገቡም። እንዲሁም በተለያዩ ማህበራዊ ኑሮ ላይ አይሳተፉም። ገና ደርግ እግሩ ከመውጣቱ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታዮች ብቅ ብቅ ማለት ሃይማኖታቸውንም በይፋ ማስፋፋት እንዲያውም ልጆችን ትምህርት ቤት ወረቀት እየሰጡ "ጌታን ተቀበሉ" ማለት ጀመሩ፡ ፡ በነባር ዕድሮችም የነበሩ አንድ ሶስት ሰዎች የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታይ ሆኑ ተባለ፡፡ እንደ ተባለውም ሰው በተገኘበት ቦታ ሁሉ ለቅሶ ቤት፣ ማርገጃ፣ ዕድር ቤት ሳይሉ የእናንተ ሃይማኖት ልክ አይደለም፤ የእኛ ልክ ነው ማለት ጀመሩ፡፡ በኋላ ነገሩ እየጠነከረ ሄዶ የዕድሮች ውስጠ ደንብ እንዲሻሻል ተደረገ። ለዚህም የኢ.ኦ.ተ.ቤ የሃይማኖት መሪዎች ሚና ነበራቸው።

የእስልምናና የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታዮች የሃይማኖት ልዩነታቸውን ወደ ጎን ትተው አንዱን ለሌላው እውቅና ሰጥቶ በመከባበር በሀዘንና በደስታ ጊዜ ለመረዳዳት የተሻለ ሀሳብ አንስተው ተስማምተው ዕድርን መሥርተው በሰላም ይኖሩ ነበር፡፡ የፕሮቴስታንት ዕምነት ተከታዮች ግን ይህን አልተገነዘቡም፡፡ ከማህበራዊ ግንኙነቱ ይልቅ ሃይማኖታቸውን ለማስፋፋት ይሰብኩ የነበረበት ዘዴና ቦታም በነባሮቹ ነዋሪዎች ላይ እንግዳ ነገር ሆነ፡፡ ይህን ለመከላከልም የዕድር ደንብ ወጣ፡፡

የወረዳው የኢ.ኦ.ተ.ቤ እና የእስልምና ሃይማኖት መሪዎች ይህንኑ ሀሳብ ያጠናክራሉ። በዕድሮች ውስጠ ደንብ ውስጥ ቀድሞ ያልነበረ የዕድር አባላትን በሃይማኖት የሚለየው አንቀጽ የገባበት ምክንያት አዲስ መጥ የሆነውን የፕሮቴስታንት ሃይማኖት መስፋፋትን ለመግታት ሲባል የተካተተ ነው።"[21] ማህበረሰቡ አዲሱን የፕሮቴስታንት ሃይማኖት መስፋፋት ለመከላከል ከዕድር ውጭ በተለያየ መልኩ እርምጃ ይወስድ ነበር። ለምሳሌ የሃይማኖቱ ተከታይ የሆኑትን ከተለያየ ማህበራዊ ግንኙነት በማግለል፤ ሲሞቱ የቀብር ቦታ በመከልከልና በመሳሰሉት ይቃወም ነበር። ከሃይማኖቱ ተከታዮች አብዛኞቹ በቤተሰብ እገዛ ስር ያሉ ወጣቶች ስለነበሩ ወላጆች ልጆችን ከቤት በማባረርና ማንኛውንም ዓይነት እገዛ በመንፈግ ተቃውሟቸውን ይገልጡ ነበር።

በዚህና በመሳሰሉት ምክንያቶች የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታዮችን ብቻ ያካተተ "አማኑኤል መረዳጃ ዕድር" በሚል ስያሜ አዲስ ዕድር አቋቋሙ፡፡ የአማኑኤል የመረዳጃ ዕድር የተቋቋመው ከአስር የማይበልጡ ነጋዴዎችና መምህራን ሁለት ሁለት ብር በየሁለት ሳምንቱ በማዋጣት በ1982 ዓ.ም መጨረሻ ነበረ። ዛሬ 217 አባላትን የያዘ ዕድር ሊሆን ችሏዋል፡፡ የተመሠረተውም በአካባቢው ሃይማኖቱን በማስተዋወቅና በማስፋፋት ከፍተኛ ሚና በነበራቸው ግለሰብ[22] አነሳሽነት ነው። የአማኑኤል የመረዳጃ ዕድር የተቋቋመው እንደ ሌሎች ዕድሮች የሞት አደጋ በደረሰ ጊዜ ለመረዳዳት ቢሆንም ዋነኛ ምክንያቱ የፕሮቴስታንት ሃይማኖትን ለማስፋፋት እንደ አንድ ዘዴ ታስቦ ነው።[23]

አንድ ሰው ወደ አማኑኤል ዕድር ለመግባት ከፈለገ ሁለት ግዴታዎችን ማሟላት አለበት። አንደኛው/ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታይ መሆኑን የሚያረጋግጥ የጽሁፍ ማስረጃ፣ ሁለተኛው/ የቅድሚያ ክፍያ ሶስት መቶ ብር መክፈል ናቸው። በእርግጥ ብዙዎቹ መተዳደሪያ ደንቦች ከቀደሙት የሙስሊም/ኦርቶዶክስ ዕድሮች ጋር ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ነው። አንዱና መሰረታዊ ልዩነት 'የሃይማኖቱ ተከታይ ነኝ' ማለት ብቻ በቂ አይደለም። …የፕሮቴስታንት ሃይማኖት

---

[21] ምንጭ፡- በትረ ትጉኃን ቀሲስ በለጠ ሀይለማሪያም፣ እድሜ 37፣ የሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ ቤተ-ክህነት ሀላፊ (ቃለ-መጠይቅ ሀምሌ 1፣ 2005)፡፡ እንዲሁም ሼህ ሙንደሲር ጠሀ፣ እድሜ 46፣ ሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ እና የበቆጂ ከተማ አስተዳደር የሸሪያ ፍርድ ቤት ዳኛና የእስልምና ጉዳዮች ተጠሪ (ቃለ-መጠይቅ ጥር 24 2007)፡፡

[22] መረጃ ሰጭ፡- አበበ ኃ/ስላሴ፣ እድሜ 52፣ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታይ፣ በመንግሥት ስራ የሚተዳደሩ የአማኑኤል ዕድር መስራችና ገንዘብ ያዥ እንዲሁም የሙሉ ወንጌል ቁጥር አንድ ቤተ-ክርስቲያን የህጻናት የሰንበት ት/ቤት አስተባባሪ፡፡

[23] የመረጃ ምንጭ፡- መጋቤ ብሩክ አለሙ እድሜ 46፣ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታይ፣ የሌሙና ቢልቢሎ ሙሉ ወንጌል ቁጥር አንድ ቤተክርስትያን፣ እንዲሁም የወረዳው የፕሮቴስታንት ሃይማኖት አስተዳዳሪ(ቃለ-መጠይቅ ሰኔ 19/2007)፡፡

ተከታይ መሆንን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ማቅረብ ግዴታ መሆኑ ነው። ይህም በመተዳደሪያ ደንቡ ተካትቷል (የአማኑኤል ዕድር 2002፣ ያለ ገፅ)፡፡ በፕሮቴስታንት ጥቅል ስም ከሚጠሩት የአማኑኤል ዕድር መሥራቾች እና አባላቱ እስከ 1992ዓ.ም "ሙሉ ወንጌል" ብቻ ነበሩ። በኋላ ግን የአምስት[24] ቅርንጫፍ የዕምነቱ ተከታዮች የዕድሮቹ አባል ሆነዋል።

ሌላው ከፕሮቴስታንት ሃይማኖት መገለል ጋር አብሮ መታየት ያለበት ጠቃሚ ጉዳይ ከ1990ዎቹ ወዲህ ሃይማኖትን መነሻ በማድረግ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ለብቻቸው ዕድር የመመስረት አዝማሚያ ተከስቶ መክሸፍ ይሆናል። ይህም፣ ምንም እንኳዋን ጉልህ ባይሆንም፣ ጥቂት የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በፈቃዳቸው ከኢ.ኦ.ተ.ቤ ምእመናን ጋር ከነበራቸው የነባር የዕድር አባልነት በተጨማሪ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይነትን እንደዋና መስፈርት አድርገው "ከክርስቲያኑ ጋር ዕድርም ሆነ ማህበራዊ ግንኙነት ሊኖረን አይገባም" የሚል አቋም በመያዝ የመሠረቱትን ዕድር ነው፡፡ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ብቻ የያዘው ጥቂት የሃይማኖቱ ተከታዮች የገነቡት ዕድር ነው። መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ይህን አቋም በያዙ የዕድር አባላት ምክንያትም ነባር ዕድሮች የተበተኑባቸው አሉ። አቶ ጀማል ዋቤ እንደህ ሲሉ ይገልፃሉ፡፡

> እኔ የነበርኩበትና ተወልጄ ያደኩበት ቀበሌ እስላሙም ክርስቲያኑም የሚገቡት ከአንድ ዕድር ነበር። በኋላ በ1995 ዓ.ም አካባቢ 'ሸሪያ ከልክሏል' ብለው ሙስሊሞች ከዕድሩ ሲወጡ የቀሩት የእስልምናና የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ዕድሩን በተኑት። እነዚህ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ክርስቲያኑ ሰርግ ደግሶ ሲጠራቸው አይሄዱም፤ እነሱም አይጠሯቸው።…በማንኛውም ማህበራዊ ሕይወት ውስጥ ከክርስቲያኖች ጋር መገናኘት አቆሙ። በእስልምና አስተምህሮ ሰበብ ሁሉም የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ባይሆኑም ጥቂቶቹ የነበረንን መተሳሰብ መሸርሸር ጀምረው ነበር፡፡ ሆኖም ይህ ልዩነት ከማህበረሰቡ አኗኗርም ሆነ ፍላጎት አብሮ ስለማይሄድና የእስልምና ሃይማኖት አስተምህሮ 'ከክርስቲያኖች ጋር የማህበራዊ ኑሮን አይፈቅድም' የሚል ትእዛዝ ስለሌለ ብዙም አልዘለቀም። የተጀመረው ልዩነት ከሸፈ፡፡[25]

የእስልምናና የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ወደ ቀድሞ አብሮነታቸው እንዲመለሱ በአካባቢው ማህበረሰብ ተቀባይነት ያላቸው የሀገር ሽማግሌዎች ትልቅ ሚና ተጫውተዋል፡፡

---

[24] አንደኛው መሠረተ ክርስቶስ ሲሆን በወረዳ ውስጥ ያለው ተከታይ ብዛት ከ30 እስከ 50 ይሆናል፡፡ ሁለተኛው መካነ ኢየሱስ ሲሆን የተከታዮች ብዛት 150 ነው፡፡ ሶስተኛው ቃለ-ህይወት ሲሆን የተከታዮች ብዛት 100 ነው፡፡ አራተኛው ህይወት ብርሃን የተከታዮች ብዛት 20 ሲሆን አምስተኛው ሙሉ ወንጌል ሲሆን ከ3000 ሺህ በላይ ቁጥር ያለውና በሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ በፕሮቴስታንት ጥቅል ስም ከሚታወቁት ትልቁን ቁጥር ይይዛል (ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቤ ብሩክ አለሙ የአርሲ ቀጠና የፕሮቴስታንት ሃይማኖት አስተባባሪ፣ ሰኔ 18 2007)፡፡

[25] መረጃ ሰጭ፡- አቶ ጀማል ዋቤ፣ እድሜ 48፣ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ፣ የዳዋ ቡርሳ ቀበሌ ሊቀመንበር የነበረ(ቃለ-መጠይቅ ጥር 16 2007)፡፡

### 3.4 ከልዩነት ወደ አንድነት

መቻቻል በሂደት የሚገነባ ተግባራዊ እሴት ነው፡፡ በመሆኑም ከላይ የተገለፁት ችግሮች ተከስተው ከቆዩ በሁዋላ የተለያዩ ሃይማኖቶች ተከታዮች ከልምድ በመማር በአንድ ላይ ሆነው የአንድነት ዕድሮችን በማቋቋም እርምት ማድረጋቸውን የመስክ መረጃዎች ያረጋግጣሉ፡፡ በመሆኑም ሃይማኖትን መሠረት ያደረጉ የዕድር የአባልነት መስፈርቶች እየተለወጡ በፕሮቴስታንትና በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች፣ በፕሮቴስታንትና በኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታዮች መካከል የነበረው አለመግባባት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየረገበ መጥቶ የአንድነት ዕድሮች እየተቋቋሙ ይገኛሉ፡፡ በተለይም ከ2003 ዓ.ም ወዲህ ተቀራርበው በመነጋገር የሃይማኖት ልዩነቶቻቸውን አክብረው በዕድር ተሰባስበው ለመረዳዳት ችለዋል፡፡

ለአንድነታቸው ማሳያ የሚሆን ከ300 በላይ አባላትን የያዘ "ሃይማኖት አልባ" ዕድር በሚል መጠሪያ በ2003 ዓ.ም ተቋቁሟል። እድሩም እስካሁን ካየነው ትልቁ ዕድር ከሚባለው ያለው ልዩነት የእድሩ አባል ለመሆን ግለሰቡ የቅድሚያ ክፍያ ከመክፈል ውጭ ሃይማኖቱ ባለመጠየቁ ነው። ከሰፈር ዕድርም ጥቂቶቹ ሃይማኖት የሚጠይቀውን መስፈርት በማሻሻል ላይ ይገኛሉ።

## 4.ማጠቃለያ እና ይሁንታ

በበቆጂ ከተማ አስተዳደር ዕድር አንድ ዋነኛ የመቻቻል ባሕርያት የሚገለፅበት የማህበራዊ ግንኙነት ተቁዋም መሆኑን፣ በተለይም ደግሞ በእስልምና እና በኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታይ ማህበረሰቦች መካከል በአብሮ መኖር ሂደት የተገነባው የመቻቻል ባህል የላቀና ልዩ ባሕርይ፣ ያለው መሆኑን አይተናል፡፡ ዕድሮችም በተለያዩ ቅርፆች፡- በፆታ፣ በመኖሪያ መንደር፣ የተደራጁ፣ ነገር ግን፣ ተመሳሳይ ሕገ-ደንቦች ያሉዋቸው፣ ዓላማቸውም በሃይማኖት ልዩነት ላይ ያልተመሠረተ በሀዘን በደስታ መረዳዳት፣ መተጋገዝ፣ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ መቻቻል እንዳለ ሁሉ አለመቻቻልም፣ በተለይም በተለያዩ ምክንያቶች ከፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታዮች ጋር በተያያዘ የተከሰተባቸው ሁኔታዎች እንደነበሩና ከጊዜ በሁዋላ ማህበረሰቡ ከልምድ በመማማር የመቻቻል መንገዶችን በመከተል ከልዩነት ወደ አንድነት ዕድሮች በመሰባሰብ የአብሮ መኖርን የወል ጥቅሞች እየተካፈለ መሆኑን ጭምር ያሳያል፡፡ ላለመቻቻሉ የሃይማኖቱ ልዩነት ሳይሆን በአካባቢው ሃይማኖቱ አለመታወቅ ወይም መጤ መሆን ነው። ስለዚህ መቻቻል አብሮ በመኖርና በመላመድ የሚገነባ ባህላዊ እሴት እንደሆነ የሚያስገነዝብ ነው።

በመቻቻል ላይ የተመሰረቱ ባህላዊ እሴቶች ለሀገር እድገት፣ ለልማት የሚበጁ ጠቃሚ መረጃዎች ናቸው። ለባህላዊ እውቀቶች ትኩረት ሰጥቶ የሚነደፍና ያለውን ተጨባጭ እውቀት አዋድዶ የያዘ ጥናት ጥናቱ ከሚሰራበት ሙያ በተጨማሪ ለተለያዩ የእውቀት መስኮች ግብአት በመሆን ያገለግላል፡፡ ስለዚህ በዚህ ጥናት መነሻነት የሚከተሉትን የይሁንታ ሀሳብ እንደሚከተለው ቀርቡዋል።

በሀገር ደረጃ ሃይማኖታዊ መቻቻልን የሚያሳዩ የወል እሴቶች ቢጠኑ፣

የዕድር መተዳደሪያ ደንቦች በተለይም የስልጣን ሽግግሩ ወደ ስልጣን የሚመጡ ግለሰቦች መስፈርትና ግዴታ ተለይቶ ቢጠና ሀገር በቀል የዲሞክራሲ እሳቤዎች ለማወቅ ያግዛሉ፣

ዕድር ለዕድርተኛው ከሚሰጠው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ባሻገር ስነልቦናዊ ጠቀሜታው ቢጠና፣

በባህላዊው መንገድ የተቋቋመው ዕድር እና ዘመናዊው የኢንሹራንስ እሳቤ በንጽጽር ቢጠና።

## **Refrences** (ዋቢ ጽሁፎች)


Alemayehu Seifu,1968; *Iddir in Addis Ababa: A sociological study*, Ethiopia Observer.

Alula, Pankhurste (ed), 2003; *Iddir participation and Development, Proceedings of the Ethiopians national Conference*.

Dejene, Ardo, 2010; An Informal Insurance Arrangement in Ethiopia; Saving & development No. 1, xxxIV.

Newman, Jay; *The Idea of Religious Tolerance,* Journal of American Philosophical Quarterly,Vol. 15, No. 3, pp 87-195, 1978.

Reat, Ross; 1983; *Insiders and Outsiders in the study of Religious Tradition*, Journal of theAmerican Academy of Religion, vol. 51, No, 3 pp. 459-476.

Shiferaw, Tesfaye; 2002; The role of civil socity Organizations in poverty alleviation, sustainable development and change: The case of Iddirs in Akaki, Nazreth and Addis Abeba; Athesis submitted to the school of graduates of addis Abeba University in partial fulfillment of the requirement for the degree of the Masters in socal Antropology.

Tomas, Leonard, 2013; Ethiopian Iddirs Mechanisms: The Case study in Pastorial Communities in Kembata & Wolita; for inter aied agricultural projects of support to family farming.

ከበቆጂ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የተገኘ ጽሑፍ፤" *ያልታተ መጥራዝ*፤ 1999።

ኪዳነወልድ ክፍሌ። 1948።*መፅሐፈ፡ ሰዋሰው፡ ወግስ፡ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ*። አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

የበቆጂ ከተማ ሁለተኛ ሸንጎ። 1988። "የመተዳደሪያ ውስጠ ደንብ።"

የበቆጂ ከተማ ምስራቃዊ ሶስተኛ ሸንጎ። 1996 "የመተዳደሪያ ውስጠ ደንብ።"

የበቆጂ ከተማ ስድስተኛ ሸንጎ። 2001። "መተዳደሪያ ደንብ።"

የበቆጂ ከተማ አስረ-ሀንደኛ ሸንጎ። "መተዳደሪያ ደንብ"፤1996

የበቆጂ ከተማ አንደኛ ሸንጎ። 2003። "መተዳደሪያ ደንብ።"

የአማኑኤል ዕድር። 2002። "መተዳደሪያ ደንብ።"

የኪዳነምህረት የሴቶች ባልትና። 1989። "መተዳደሪያ ደንብ።"

የገብርኤል የሴቶች ባልትና። 1998። "መተዳደሪያ ደንብ።"

ፍሬሕይወት ባዩ። 2000። "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ንዋያተ ቅድሳት ሃይማኖታዊና ፎክሎራዊ ገጽታ።" ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለ ኤም ኤ. ዲግሪ ማሟያ፤ በኢትዮጵያ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።